www.abyssinialaw.com



9ኛ አመት ቁጥር 52
9th Year No 52

ባህር ዳር ____ ቀን 1996 ዓ.ም
Bahir Dar _____, 2004

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

# ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE HIG

## OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA


| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር<br>**Price** | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | **ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE** | የፖ.ሣ.ቁ<br>**P.o. Box** ***312*** |


| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| ደንብ ቁጥር 3/1995 ዓ.ም | Regulation No. 3/2002 |
| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ምት የክልል መስተዳድር ም/ቤት አደረጃጀት፣ ስብሰባና ውስጣዊ የአሰራር ሥነ-ሥርዓት መወሰኛ ደንብ | The Amhara National Regional State, Organization of the Regional Government Council, Determination of its Meeting and Internal Rule of Procedure Regulation. Page 22 |

## ደንብ ቁጥር 3/1995 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የክልል መስተዳድር ም/ቤቱን አደረጃጀት፣ ስብሰባና ውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት ለመወሰን የወጣ ደንብ፡

## REGULATION NO. 3/2002

A REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE ORGANIZATION OF THE REGIONAL GOVERNMENT COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL NREGIONAL STATE AND DETRMINATION OF ITS MEETING AND INTERNAL WORKING PROCEDURE.

www.abyssinialaw.com



የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ም/ቤት በብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ ከፍተኛ የአስፈፃሚነት ስልጣን የተሠጠው አካል እንደመሆኑ መጠን ተሻሽሎ በወጣው የ1994 ዓ.ም የክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 58 ድንጋጌዎች ስር የተጣለበትን ባለብዙ ፈርጅ ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት የቅድሚያ የመወያያ አጀንዳዎችን እየቀረፀና በአባላቱ እያስፀደቀ በየጊዜው መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን በማካሔድ በክልሉ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ዙሪያ በንቃት መምከር፣ መከራከርና ውሣኔዎችን ማሳለፍ የሚጠበቅበት በመሆኑ፤

WHERE AS, the Amhara National Regional Government Council, as an organ given the highest executive power by the National Regional State, and to effectively discharge the multifaceted responsibility trusted to it under the provisions of Article 58 of the Regional Constitution revised and issued in the year 2001, is supposed to exchange views, debate and pass decisions on the soci-economic, political and administrative issues of the region formulating prediscussion agenda, getting them endorsed by its members and conducting ordinary as well as extra ordinary meetings;

ለዚህም ይረዳው ዘንድ ም/ቤቱ በሚገባ ተደራጅቶ መደበኛ ስብሰባዎች የሚካሄዱባቸውን ጊዜያት፣ ስብሰባው የሚመራበትን፣ ውይይቶች የሚደረጉበትንና ውሣኔዎች የሚተላለፉበትን ውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት መወሰኛ ደንብ አውጥቶ በአፋጣኝ ሥራ ላይ ማዋል የማይታለፍ ግዴታ በመሆኑ፤

WHERE AS, to this effect, it has become an impassable duty for the council to issue and promptly bring in to force a regulation for the organization of the council and determination of its times of ordinary meetings, internal working procedure for directing the meeting, conducting the discussions and passing decisions;

የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱን አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀትና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም አንቀጽ-26 ሥር በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል::

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region Government pursuant to the power vested in it under art. 26 of proclamation No. 60/2001 issued for the reorganization of executive organs of the Amhara National Regional State and the determination of their respective powers and duties, hereby issues this regulation:

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የክልል መስተዳድር ም/ቤት

### 1. Short Title

This regulation may be cited as ”The Organization of the Regional Government

www.abyssinialaw.com



አደረጃጀት፣ ስብሰባና ውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት መወሰኛ ደንብ ቁጥር 3/1995 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

1. "የክልል መስተዳድር ም/ቤት" ማለት በ1994 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 57 ንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ ከፍተኛ አስፈፃሚ አካል ነው::
2. "ርዕሰ መስተዳድር" ማለት በዚሁ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 60 ንኡስ አንቀጽ 1 ሥር የተጠቀሰው አካል ነው::
3. "ምክር ቤት" ማለት ከዚህ በላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተጠቀሰው የክልል መስተዳድር ም/ቤት ነው::

# ክፍል ሁለት
# ስለ ምክር ቤቱ ተዋጽኦ፣ ሥልጣን፣ አደረጃጀትና አሠራር

## 3. ስለ ም/ቤቱ አባላትና ምትክ አባላት

1. የክልል መስተዳድር ም/ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል::

ሀ/ ርዕሰ መስተዳድር፣

ለ/ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር፣

ሐ/ የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱን

Council of the Amhara National Regional State, and the Determination of its Meeting and Internal Working Procedure Regulation No. 3/2002."

## 2. Definitions

Unless the context requires otherwise, in this regulation:

1. "Council of the Regional Government" means the highest executive organ of the Amhara National Regional State established pursuant to the provisions of Art. 57, sub art. 1 of the 2001 revised constitution of the State.
2. "Head of Government" means the organ referred to under art. 60, sub art 1 of the constitution.
3. "Council" means the council of the Regional Government indicated hereinabove under this article.

# PART TWO
# COMPOSITION, POWER, ORGANIZATION AND WORKING PROCEDURE OF THE COUNCIL

## 3. Members and Substitute Members of the Council

1. Council of the regional government shall constitute the following members:

a. the head of government;

b. the deputy head of government;

c. the top most heads of bureaux

www.abyssinialaw.com



አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀትና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁርጥ 60/1994 አንቀጽ 3 ስር የተቋቋሙትን የቢሮዎች የበላይ ኃላፊዎች፣

መ/ በአዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ/ም አንቀጽ 3 ሥር ከተጠቀሱት ቢሮዎች ውጭ ርዕሰ መስተዳድሩ የምክር ቤት አባላት እንዲሆኑ በተለይ የመረጣቸው ሌሎች የቢሮ ኃላፊዎችና ባለሥለጣኖች::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 /ሐ/ ሥር የተመለከተው ማንኛውም የቢሮ ኃላፊ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ ምክትሉ ወይም ከአንድ በላይ ምክትሎች ካሉ በግልጽ ተለይቶ ቋሚ የጽሁፍ ውክልና የተሰጠው ምክትል በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በምትክ አባልነት ይሳተፋል::

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው ምክትል እንደአግባቡ በቀዳሚ ምክትል ወይም በምክትል ቢሮ ኃላፊ ደረጃ የተሾመ ሊሆን ይችላል::

## 4. ስለ ምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

1. የክልል መስተዳድር ምክር ቤት በከፍተኛ የክልሉ መንግሥታዊ ጉዳዮች ላይ በጋራ የሚመክርና ግምገማዎችን የሚያካሂድ የበላይ አስፈፃሚ አካላት ኃላፊዎች የወል መድረክ ሲሆን የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ ማዕከላዊ አስፈፃሚና ውሣኔ ሰጭ አካል ነው:: በዚህም መሠረት ምክር ቤቱ ተሻሽሎ በወጣው የብሔራዊ ክልሉ

established under art. 3 of proclamation No. 60/2001 for the Reorganization of the National Regional State Executive Organs and Determination of their Powers and Duties;

d. other bureau heads and officials thereof outside the list of those indicated under art. 3 of proclamation No. 3/2001 selected specifically for membership in the government council by the head of government.

2. Whenever any bureau head, referred to under this article, sub article 1 (c), is unable to attend a meeting of the council thereof, his deputy head or in the case of presence of more than one deputies, the deputy specifically designated by an express authorization may be able to participate as a substitute member by proxy in the said meeting of the council.

3. The deputy referred to in this article, sub article 2 might have been appointed as a senior deputy or deputy bureau head.

## 4. Powers and Duties of the Council

1. The council of the regional government, as the common forum for the highest heads of executive organs consulting and undertaking evaluations collectively on the highest regional state issues, is the central executive and decision-making body. The council shall have powers and duties vested in it pursuant to article 58 of revised issue of the

www.abyssinialaw.com



ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 58ና በሌሎች ሕጐች የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ ፡-

ሀ/ የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ የበላይ አስፈፃሚ አካላትን ዓመታዊ የሥራ እቅድ ገምግሞ ያፀድቃል፣ የሥራ አፈፃፀማቸውንም በየሩብ ዓመቱ ከእቅዳቸው አንፃር እየገመገመ አስፈላጊውን መመሪያና ትዕዛዝ ይሰጣል፤

ለ/ በፖሊሲ ነክ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ አዳዲስ ፖሊሲዎችን ያወጣል፣ ነባሮቹንያሻሽላል፤

ሐ/ ከአስፈፃሚ አካላት መንጭተውና ተረቀው በሚቀርቡለት አዳዲስ ሕጐች ወይም የነባር ሕጐች ማሻሻያዎች ላይ መክሮ ውሣኔዎችን ያሳልፋል፣ ሠነዶቹን እንዲፀድቁ በደረጃው ለብሔራዊ ክልሉ ሕግ አውጪ ምክር ቤት በወቅቱ ያስተላልፋል፤

መ/ በራሱ ደረጃ ተመክሮባቸው በሚወጡ ረቂቅ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ ተወያይቶ ያፀድቃል፤

ሠ/ የምክር ቤቱ አባላት በውጭ ሃገር ሊያካሂዱት ስለአቀዱት የሥራ ጉብኝት ተወያይቶ መመሪያ ይሰጣል፣ ከጉብኝቱ መልስም በሚቀርብለት ሪፖርት ላይ ይወያያል፤

National Regional Constitution, and in other laws.

2. Without prejudice to the general explanation indicated in sub. article of this article, the council shall:

a. evaluate and approve the annual work-plan of the highest executive organs of the National Regional State, evaluate their performance quarterly in respect to plan, give a necessary guide and order;

b. formulate new policies having discussed policy-related issues, update the existing ones as well;

c. pass decisions, exchanging views, on newly emanated draft laws or the amendments of existing ones, transfer the documents to the National Regional legislative council hierarchically for approval;

d. discuss on and approve draft regulations as well as directives which are to be consulted up on and issued at its level;

e. discuss and give direction regarding working visit members of the council have planned to conduct abroad, exchange views on the report submitted to it after the return from visit;

www.abyssinialaw.com



ረ/ የውጭ ሃገር ልዑካን ቡድኖች በክልሉ ውስጥ ለሚያደርጉት የሥራ ጉብኝት እንደአስፈላጊነቱ እየተወያየ ለሚመለከታቸው የምክር ቤቱ አባላት መመሪያ ይሰጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜም የልዑካን ቡድኑ አባላት በተልዕኮ ዙሪያ የሚያቀርቡለትን ዘገባ አዳምጦ ውሣኔ ይሰጣል፣

ሰ/ በሕገ መንግሥቱ፣በአዋጅ ቁጥር 60/1994 እና በሌሎች ሕጐች በተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ውስጥ በሚጠቃለሉ፣ በከፍተኛ የክልሉ አስፈፃሚና አስተዳደራዊ አካልነቱ ሣቢያ ይመክርባቸው ዘንድ አስፈልገው የምክር ቤት አባላት በሚያቀርቧቸውና ከርዕሰ መስተዳድሩም ሆነ ከብሔራዊ ክልሉ ምክር ቤት በሚመሩ ጉዳዮች ላይ ይወያያል፣ ውሣኔዎችን ያሣልፉል፣ መመሪያዎችን ይሰጣል::

3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩ ነው::

4. የክልል መስተዳድር ምክር ቤቱ በወል በሚያሳልፋቸው ውሣኔዎችና ለሚፈፀማቸው ተግባራት ሁሉ ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ክልሉ ምክር ቤት ይሆናል::

5. ምክር ቤቱ ለሚያከናውናቸው ተግባራት አፈፃፀም በአግባቡ የሚመራበትን የራሱን ዝርዝር የውስጥ መመሪያዎች በየጊዜው ሊያወጣ ይችላል:: ሆኖም ርዕሰ መስተዳድሩ የምክር ቤቱ ሰብሳቢ እንደመሆኑ መጠን አሠራሩን አስመልክቶ የመጨረሻ ውሣኔ ሰጭ መሆኑ የተጠበቀ ነው::

f. discuss, as required, a working visit, foreign missions are to conduct in the region, give direction to concerned members of the council; whenever found necessary, it shall also take a decision hearing the report members of the mission submit about their mission;

g. discuss, pass decisions and give directives on issues comprised in powers and duties vested to it pursuant to the constitution, proclamation No. 60/2001 and other laws; same submitted by members and administrative organ, and those issues directed to it by head of the government or the National Regional Council.

3. The Regional Government Council shall be accountable to the head of government.

4. The Regional Government Council shall also be accountable to the National Regional Council for decisions it passes and duties it executes in common.

5. The council can occasionally issue its own detailed internal directives by which it is to be guided in the implementation of duties it performs, provided, however, that giving the final decision with regard to the conduct of the council is the preserve of head of government, as a chairperson of the council.

www.abyssinialaw.com



## 5. ስለ ምክር ቤቱ አደረጃጀትና አቋም

1. ምክር ቤቱ ለሥራው በሚያስፈልገው አኳኋን ራሱን በቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ከፋፍሎ ሊያደራጅ ይችላል፡፡ ያም ሆኖ በሥልጣኑ ሥር በሚጠቃለሉ ጉዳዮች ላይ ውሣኔዎችን የሚያሳልፈው በጋራ ምክክርና ውይይት ይሆናል፡፡
2. የምክር ቤቱ ጽ/ቤት የርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት ነው፡፡

## 6. ስለ ምክር ቤቱ ኃላፊነትና የአሠራር መርሆዎች

1. የክልል መስተዳድር ምክር ቤት የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ ማዕከላዊ አስፈፃሚና ከፍተኛ ውሣኔ ሰጪ አካል ሲሆን የክልሉን መንግሥት ፖሊሲዎች የመንደፍና ሲፀድቁም አተገባበራቸውን በበላይነት የመምራት፣ የመከታተልና የማስተባበር ኃላፊነት አለበት፡፡
2. ምክር ቤቱ የሚያሳልፋቸው መንግሥታዊ ውሣኔዎች ሁሉ መላ አባላቱ በእኩልነትና በነፃነት ሃሳብ የተለዋወጡባቸውና የመከሩባቸው ይሆናሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚተላለፉትን ውሣኔዎች መላው የምክር ቤቱ አባላት እንደክልሉ መንግሥት ፖሊሲ የማክበርና የማስከበር የወል ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፡፡
3. ማናቸውም ጉዳዮች ለምክር ቤቱ ውሣኔ ከመቅረባቸው በፊት አቅራቢው የምክር ቤቱ አባል አግባብ ያላቸውን ሌሎች አካላት በቅድሚያ ማማከርና የሚኖራቸውን አስተያየት ተገቢነቱን መዝኖ ማካተት ወይም ማስተናገድ የሚጠበቅበት ሲሆን

## 5. Organization and Status of the Council

1. The council may organize itself dividing, as it may be necessary for its duty, into standing and provisional committees; provided, however, that it shall pass decisions on matters under its authority in joint consultation and discussion.
2. Office of the government council is that of Head of the Government.

## 6. Responsibility and working Principles of the Council

1. The regional government council, as the central executive and highest decision making organ of the National Regional State, shall have the responsibility of drafting policies of the regional state, and directing over, monitoring and coordinating their implementation.
2. All governmental decisions, the council take, shall be of what all the members exchanged ideas and discussed on equally and freely. All members of the council shall have a common responsibility and obligation to respect the decisions made this way and to have them respected as policies of the region.
3. Before any topics are submitted to the council for discussion, the member submitting the topic to the council is expected to consult any other appropriate bodies in advance, and incorporate or entertain their proposal weighing its

www.abyssinialaw.com



ይህም የምክር ቤቱ አንድ ቋሚ የአሠራር ዘይቤ ይሆናል፡፡

4. ምክር ቤቱና በሥሩ የተዋቀሩ አደረጃጀቶች የሚያደርጓቸው ውይይቶች እንዲሁም ከእነዚሁ ጋር የተዛመዱ ሠነዶች ሁሉ በምስጢር ይያዛሉ፣ ይጠበቃሉ፡፡

5. የምክር ቤቱ የውሣኔ አሰጣጥ በተሟሉ መረጃዎች ላይ የተመረኮዘና የሕዝብን ጥቅም ያገናዘበ ይሆን ዘንድ የሚቀርቡለት መነሻ መግለጫዎችና አማራጭ፣ የውሣኔ ሃሳቦች /የታመነበት አማራጭ ተለይቶ/ በበቂ እውቀት ላይ የተመሠረተ ውሣኔ ለመስጠት የሚያስችሉ መረጃዎችን ሁሉ ያካተቱና በከፍተኛ የጥራት ደረጃ የተዘጋጁ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

6. በምክር ቤቱ የሚተላለፉ ማናቸውም ውሣኔዎች አግባብ ያላቸው ፍሬ ነገሮች ሁሉ በጥልቀት መፈተሻቸውንና ከመንግሥት ፖሊሲም ሆነ አሠራር ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን የሚያንፀባርቁ ይሆናሉ፡፡

7. የምክር ቤቱ አባላት በአንድ ዓይነት የአሠራር ሕጐችና በከፍተኛ ደረጃ የዓላማ ጽናት የሚንቀሳቀሱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ የምክር ቤቱ የአሠራር ሂደቶች በመላ በርዕሰ መስተዳድሩ ይመራሉ፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለ ምክር ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ተግባር

### 7. ስለ ምክር ቤቱ አመራር

1. የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ርዕሰ መስተዳድሩ

relevance, this shall be a permanent working style.

4. Discussions conducted by the council and the organizations structured under the council, as well as documents related to them shall be handled and kept in secrecy.

5. Decision making processes of the council to be based upon complete information and to be considerate of public benefit, initial statements and alternate proposals (with credible preference) submitted to the council should incorporate information that enable it to give decision based on sufficient knowledge, and be prepared with the highest quality level.

6. Any decisions passed by the council shall reflect that all appropriate main ideas have been go through and they are in harmony with government policy, procedure as well.

7. All working process of the council shall be led by head of the government to be able to ensure that all members of the council act with high level of holding firm to their goal and using uniform working rules.

## PART THREE

## DUTIES OF HEADS OF THE COUNCIL

### 7. Management of the Council

1. Head of the Government shall be chairman

www.abyssinialaw.com



ነው::

2. ርዕሰ-መስተዳድሩ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ ም/ቤቱ የሚመራውና የሚሰበሰበው በምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል::

3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ና 2 ሥር የተመለከቱት የምክር ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ሁለቱም በማይኖሩበት ወይም ሥራቸውን ለማከናወን በማይችሉበት ጊዜና ሁኔታ ም/ቤቱ የሚመራው በሰብሳቢው በሚወከል አባል ይሆናል::

of the council.

2. In the absence of Head of the government or under circumstances where he is unable to perform his normal duties, the council shall be led and called for a meeting by the deputy head of the government.

3. When the two heads of the council, referred to under this article, sub article 1 and 2, are absent or under circumstances when they are unable to perform their duties, the council shall be chaired by a member whom the chairman has delegated.

## 8. የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

የምክር ቤቱ ሰብሳቢ:-

1. የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይጠራል፣ ይመራል፣ ምክር ቤቱን ይወክላል፣ ሥራዎቹን ያስተባብራል፤
2. ይህንን ደንብና የም/ቤቱን አጠቃላይ ሥነ-ሥርዓታዊነት ያስከብራል፤
3. በምክር ቤቱ ውሳኔ መሠረት በስብሰባዎች ላይ በአስረጅነት ቀርበው ማብራሪያ እንዲሰጡ የሚፈለጉ ባለሥልጣኖችና ሌሎች ኤክስፐርቶች ቢኖሩ ተገቢው ጥሪ ደርሷቸው በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ያደርጋል፤
4. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ምክር ቤቱ በተወያየባቸው ጉዳዮች ላይ ድምጽ እንዲሰጥ ያደርጋል፤
5. የምክር ቤቱን ውሳኔዎችና መመሪያዎች ተፈፃሚነት ይከታተላል፤
6. በስብሰባው ሂደት ወቅት የተናጋሪዎችን ቅደም ተከተል ይይዛል፣ የመናገር

## 8. Duties and Responsibilities of Chairperson of the Council

The chairperson of the council shall:

1. call the meetings of the council, chair them, represent the council and coordinate the actions of this body;
2. have this regulation and general procedure of the council be respected;
3. summon officials and other experts who are required to give further explanation as an informant, if any, to appear at the meeting of the council;
4. cause the issues discussed by the council to be voted whenever it is found out to be necessary;
5. monitor the implementation of the decisions and directives of the council;
6. record the sequence of the speakers, grant or prohibit the chance to talk and stop

www.abyssinialaw.com



እድል ይሰጣል፣ ይከለክላል፣ ጣልቃ የሚገቡ ቢኖሩም ያስቆማል፡፡

those who are interfering.

## 9. ስለምክር ቤቱ ጽ/ቤት ኃላፊ

1. በአዋጅ ቁጥር 65/1994 እና በዚህ ደንብ መሠረት የርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት ኃላፊ የምክር ቤቱ ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆን ጭምር ይሠራል፡፡
2. የምክር ቤቱ ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩ ሆኖ የምክር ቤቱን ሥነ-ሥርዓት፣ የኦፐሬሽንና የሎጀስቲክስ አገልግሎት በመምራት ለምክር ቤቱ ተግባሮች ቀጣይነትና አስተማማኝነት ድጋፍ የመስጠት አጠቃላይ ሚና ሲኖረው ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቱ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

   ሀ/ የምክር ቤቱን ጽ/ቤት በኃላፊነት ይመራል፣ ሠራተኞቹን ያስተዳድራል፤

   ለ/ በምክር ቤቱ ጽ/ቤት ስም ከመንግሥታዊና አስፈላጊ ከሆኑ ሌሎች አካላት ጋር ይፃፃፋል፤

   ሐ/ የምክር ቤቱን የሥራ ፕሮግራሞችና የውይይት አጀንዳዎች በማቀነባበር ረገድ ለምክር ቤቱ ሰብሳቢ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

   መ/ በምክር ቤቱ ሰብሳቢ ተቀባይነት የተሰጠው የውይይት አጀንዳና ለዚሁም የቀረቡ ሠነዶች በወቅቱ ተባዝተው ለምክር ቤቱ አባላት መሠራጨታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

   ሠ/ በምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይ በአካል

## 9. Head of the Office of the Council

1. In accordance with proclamation No.65/2002 and this regulation, head of office of head of the government shall act as head of office of the council, too.
2. Head of office of the council, being accountable to Head of the regional government, has the general role of giving support to the council for the continuity and reliability of its activity by guiding the procedure, the operation, the logistics service of the council. Detailed duties and responsibilities of the head of office of the council include the following. He/she shall:

   a. direct over office of the council, administer the employees;

   b. correspond with governmental and other parties, as it may be necessary, on behalf of office of the council;

   c. render the necessary support to the chairperson in organizing the agenda, work plan of the council as well;

   d. monitor and control that the agenda approved by head of the council and documents submitted for this purpose have been duplicated and handed out to members of the council in time;

   e. appearing in person at the meeting of

www.abyssinialaw.com



እየተገኘ ቃለ ጉባዔዎችና ውሣኔዎች ለዚሁ በተመደበው የጽ/ቤቱ ባልደረባ በትክክል መያዛቸውን ያረጋግጣል፣ ቃለ ጉባዔዎቹም በምክር ቤቱ አባላት ከፀደቁ በኋላ ሰብሳቢውን በማስፈረምና ራሱም በመፈረም በሥርዓት መቀመጣቸውና መጠበቃቸውን ይቆጣጠራል፤

ረ/ የምክር ቤቱ ውሣኔ ምስጢርነቱ ተጠብቆ ለሚመለከታቸው በወቅቱ መድረሱን ያረጋግጣል፣ አባላት በጽሁፍ ጥያቄ ሲያቀርቡም በወቅቱ ተገልብጠ ትክክለኛነቱ ተረጋግጦና ተፈርሞ እንዲሰጣቸው ያደርጋል፤

ሰ/ ለምክር ቤቱየሚቀርቡ ጉዳዮች በዚህ የውስጥ ደንብ የተገለፀውንና ምክር ቤቱ ወይም ሰብሳቢው የሚያስቀምጧቸውን የይዘትና የጥራት ደረጃዎችና መሥፈርቶች አሟልተው መቅረባቸውን ያረጋግጣል፤

ሸ/ የምክር ቤቱ የሰብሰባ አዳራሽ በሚገባ መደራጀቱንና በምክር ቤቱ አባላት ለሥራ የሚፈለጉ ቦታዎችና ቁሳቁሶች ተሟልተው መገኘታቸውን ያረጋግጣል፤

ቀ/ ምክር ቤቱ የተለየ መመሪያ ካልሰጠ በስተቀር የምክር ቤቱ ዜና መዋእል በየጊዜው በዜና መሠራጫዎች ለሕዝብ እንዲገለጽ ያደርጋል፤

በ/ በምክር ቤቱ ወይም በሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች የምክር ቤቱን ተግባራትና ተዛማች ሥራዎች ያከናውናል::

the council, ensure that minutes and discussions have been properly taken by a fellow worker assigned to do so, control also if the minutes are preserved and kept orderly after getting the approval of members of the council and signed by the chairperson and himself.

f. make sure that the decision of the council, kept secret, reaches concerned bodies in time, make the decision immediately get copied, its accuracy approved, signed and be given to members on their inquiry submitted in writing;

g. make sure that issues that are presented to the council have been fulfilling content and quality standards and criteria indicated in this inhouse regulation and set by the council or the chairperson;

h. ensure that the conference hall of the council has been properly arranged, the rooms and materials required by members of the council for work are found complete;

i. cause the publication of the activity of the council occasionally through newscasts;

j. perform other activities of the council and related duties assigned to him by the council or chairperson.

www.abyssinialaw.com



## ክፍል አራት

## የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

### 10. ስለስብሰባ

1. አስቸኳይ ስብሰባዎች እንዲያካሂድ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ካልተፈጠሩ በስተቀር ምክር ቤቱ በሳምንት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል::
2. የምክር ቤቱ አስቸኳይ ስብሰባ በሰብሳቢው ውሣኔ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት ሲጠይቁ ሊጠራ ይችላል::

### 11. የሥራ ሰዓት

ምክር ቤቱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር የምክር ቤቱ የሥራ ሰዓት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሥራ ሰዓት ይሆናል::

### 12. አቀማመጥ

የምክር ቤቱ አባላትና ሌሎች በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ እንዲገኙ የተፈቀደላቸው ሰዎች የምክር ቤቱ ጽ/ቤት ኃላፊ በሚመድባቸው ቦታ ይቀመጣሉ::

### 13. ስለጉዳዮች አቀራረብ

1. ለምክር ቤቱ የሚቀርብ ማናቸውም ጉዳይ:-
   ሀ/ የጉዳዩን ፍሬ ነገር፣ የጥናቱን አስተዋጽኦና ውሣኔ እንዲሰጥባቸው የሚያስፈልጉትን ነጥቦች የያዘ መግለጫ፤
   ለ/ የሕግ ረቂቅ ከሆነ ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀውን ረቂቅና የሕጉን መንፈስ የሚያስረዳ አጭር መግለጫ አጠቃልሎ መቅረብ አለበት::

## PART FOUR

## MEETING PROCEDURES

### 10. Meeting

1. Unless conditions that are compelling to have an extra ordinary meeting are created, the council shall have ordinary meeting once a week.
2. An extra ordinary meeting may be called either by the decision of the chairperson or the inquiry of one-third of the council members.

### 11. Working Hour

Provided that it is not decided in a special way, the working hour of the council shall be that of the government offices.

### 12. Seating

Members of the council as well as other people allowed to appear at the meeting of the council shall take a seat where the head of office of the council tell them to do so.

### 13. Presentation of Issues

1. Any issue presented to the council shall:
   a. be a statement consisting of the main point of the issue, the contribution of a study and the points required to be decided on;
   b. be presented comprising the Amharic draft law and short explanation that clarifies the concept of the law, if it is a draft law.

www.abyssinialaw.com



2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ /1/ የተመለከቱት መግለጫዎች የምክር ቤቱ ሰብሳቢ በሚወስነው መሠረት በበቂ ቅጅ ተዘጋጅተው መቅረብ ይኖርባቸዋል::
3. ጉዳዮች ለምክር ቤቱ በቀረቡበት የጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት እየታዩ በምክር ቤቱ ሰብሳቢ በኩል ለውይይት ሊቀርቡ ይችላሉ::
4. ምክር ቤቱ ወይም ሰብሳቢው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በቀረበው ጉዳይ ላይ ውይይት ከመደረጉ በፊት አግባብ ባለው የምክር ቤቱ ንኡስ ኮሚቴ እንዲጠና ሊያደርግ ይችላል::

2. Statements indicated in sub article 1 of this article shall be presented in enough copies as decided by the chairperson of the council.
3. Topics of discussion can be put forward for discussion through the chairperson of the council according to the chronological order of their submission to the council.
4. If the council or the chairperson finds it necessary, he may have the submitted topic of discussion be reviewed by and appropriate sub-committee of the council before a discussion is made on it.

## 14. ስለአጀንዳ መጽደቅ

1. የምክር ቤቱ አጀንዳ ከስብሰባው ሦስት ቀናት ቀደም ብሎ ለምክር ቤቱ አባላት መላክ አለበት::
2. ምክር ቤቱ የእለቱን አጀንዳ እንደ ጉዳዩ አስቸኳይነትና ክብደት በአባላቱ አንድ ሦስተኛ ድምጽ ያፀድቃል፣ ቅደም ተከተሉንም ይወስናል::
3. በምክር ቤቱ የመወያያ አጀንዳዎች ቅደም ተከተል አወሳሰን:-

ሀ/ በሰብሳቢው አማካኝነት የቀረበ አስቸኳይ ጉዳይ፤
ለ/ ምክር ቤቱ በተከታዩ የስብሰባ ጊዜ እንዲታዩ ቀደም ሲል በቀነ-ቀጠሮ ያስተላለፋቸው ጉዳዮች፤
ሐ/ በአባላቱ ቀርቦ በምክር ቤቱ አንድ ሦስተኛ ድምጽ የተደገፈ ጉዳይ፤
መ/ ምክር ቤቱ በንኡሳን ኮሚቴዎች እንዲጠኑ አስቀድሞ ውሣኔ የሰጠባቸው

## 14. Endorsement of Agenda

1. The agenda of the council shall be sent to all members of the council three days a head of the meeting.
2. The council shall approve the agenda of a day and decide their sequence according to the urgency and weight of the issue by a one-third vote of the members.
3. In determining the sequence of discussion topics, the following shall be given priority:
   a. urgent issue presented through the chairperson;
   b. subjects that the council has adjourned beforehand to be viewed in a subsequent meeting time;
   c. a topic presented by the members and endorsed by one-third vote;
   d. issues the council has taken decision on in advance to be reviewed by a

www.abyssinialaw.com



ጉዳዮችና፤

ሠ/ የምክር ቤቱ ንኡሳን ኮሚቴዎች የሚያቀርቧቸው ዘገባዎች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል::

## 15. ምልዓተ-ጉባዔ

1. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት ከተገኙ የምክር ቤቱ ስብሰባ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል::
2. ምልዓተ-ጉባዔ መኖሩን የጽ/ቤት ኃላፊው ሲያረጋግጥለት የምክር ቤቱ ሰብሳቢ ምክር ቤቱ ሥራውን እንዲጀምር ያደርጋል::

## 16. ውይይት ስለመጀመር

1. በአንድ ጉዳይ ላይ ውይይት መካሄድ የሚጀመረው ጉዳዩን ያጠናው አካል ቢኖር የሚያቀርበውን አጭር መግለጫ ወይም ማብራሪያ አስቀድሞ በማዳመጥ ይሆናል::
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ /1/ መሠረት መግለጫው ካበቃ በኋላ በጉዳዩ ላይ እንደአስፈላጊነቱ ውይይት ይከፈታል::

## 17. ስለተናጋሪዎች ቅደም ተከተል

1. አንድ አባል ለመናገር ሲፈልግ እጁን በማንሣት ለሰብሳቢው ማመልከት አለበት::
2. ሰብሳቢው እንደ እጅ አወጣጡ በሚይዘው ዝርዝር መሠረት የተናጋሪዎችን ቅደም ተከተል ይወስናል::
3. አንድ አባል በሰብሳቢው ተፈቅዶለት በመናገር ላይ እያለ ሌላ አባል ሊያቋርጠው አይችልም፤ ሆኖም ውይይቱ ፈር ለቋል

sub-committee; and

e. reports the sub-committee has submitted.

## 15. Quorum

1. Of all members of the council, the presence of the two-third at a meeting shall have a quorum.
2. The chairperson of the council shall make the council start its duty whenever the head of office of the council assures him of the achievement of the quorum.

## 16. Commencement of Discussion

1. Undertaking a discussion on an issue shall commence by the prior hearing of a short explanation or a clarification, if any, presented by the body who has studied the issue beforehand.
2. According to this article, sub-article 1 of this regulation, a discussion on the issue shall be opened after the explanation/the clarification, as required.

## 17. Sequence of Speakers

1. Any member of the council shall raise and show his hand to the chairperson if he wants to speak.
2. The chairperson shall determine the sequence of the speakers according to the time of their hand raising.
3. A member is not allowed to interrupt another member speaking with permission; provided, however, that the

www.abyssinialaw.com



ወይም ሥነ-ሥርዓት ተጊድሏል ብሎ ለማመልከት ወይም መረጃ ለመስጠት ለሚጠይቅ አባል ስለ "ደንብ" ወይም "መረጃ" ሲል ሰብሳቢው ተራ ጠብቆ እንዲናገር እድል ይሰጠዋል፣ ሆኖም የደንብ ጥያቄ ከሁሉም ይልቅ ቅድሚያ ይሰጠዋል፣ መረጃና ማብራሪያ ደግሞ እንደቅደም ተከተላቸው ይቀርባሉ::

4. የሚከተሉትን በሚመለከት የሚቀርቡ ሀሣቦች ከማናቸውም የውሣኔ ሀሣብ ወይም የማሻሻያ ሀሣብ ቅድሚያ ይኖራቸዋል:-

ሀ/ ጉዳዩ እንደገና እንዲጠና፤

ለ/ ጉዳዩ ላልተወሰነ ጊዜ እንዲተላለፍ፤

ሐ/ ስብሰባው በቀጠሮ እንዲተላለፍ፤

መ/ በጉዳዩ ላይ የሚደረገው ክርክር እንዲያድር፤

ሠ/ ውይይቱ ወደሚቀጥለው ጉዳይ እንዲተላለፍ፤

ረ/ በጉዳዩ ላይ የሚደረገው ክርክር እንዲያበቃ የሚቀርብ ሀሣብ::

## 18. አስረጂዎችን ስለመጥራት

ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማብራሪያ እንዲሰጡ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ባለስልጣኖችና ሌሎች ግለሰቦች ጠርቶ ለማነጋገር ይችላል::

## 19. የውሣኔ ሀሣብ ስለማቅረብ

1. ሰብሳቢው በጉዳዩ ላይ በቂ ውይይት ተደርጎበታል ብሎ ሲያምን የውሣኔ ሀሣብ ለማቅረብ ወይም በምክር ቤቱ አባላት እንዲቀርብ ለመጠየቅ ይችላል::

chairperson, for the sake of ”procedure” or ”information” shall grant a person who wants to show disorder of the discussion, or violation of procedure a chance to talk in his turn; still, however, the question for an orderly procedure shall be given a priority to all others, information and clarification shall be presented in their respective order.

4. Proposals regarding the following shall be given priority to other issues or amendments:

a. reconsidering the topic;

b. putting off an issue for an unlimited period;

c. adjourning a meeting by an appointment;

d. postponing a debate overnight;

e. going on to discuss the next issue;

f. ending the debate on the issue.

## 18. Calling Informants

Whenever the council finds it essential, it may call and talk to authorities and other individuals, concerned with the issue, for clarification.

## 19. Forwarding a Motion

1. When the chairperson believes that sufficient discussion has been made on a problem, he may either forward a motion by himself or ask for same to be proposed

www.abyssinialaw.com



by any other members of the council.

2. የውሣኔ ሀሣብ በቃል ወይም በጽሑፍ ሊቀርብ ይችላል፡፡
3. የቀረበው የውሣኔ ሀሣብ ቢያንስ በአንድ ሌላ አባል ከተደገፈ ድምጽ ይሰጥበታል፡፡
4. በጉዳዩ ላይ ከአንድ በላይ የሆኑ የውሣኔ ሀሣቦች የቀረቡ እንደሆነ በድምጽ ብልጫ ይለያሉ፡፡
5. ድምጽ እንዲሰጥ የሚጠየቅበት ተራ በቅድሚያ ለድጋፍ ቀጥሎ ለተቃውሞ በመጨረሻም ለተአቅቦ ይሆናል፡፡

2. A motion can be proposed orally or in writing.
3. If the motion proposed is seconded by at least another member, it shall be voted.
4. Incase, more than one motions are proposed on a subject, one of them shall pass by a majority vote.
5. As to the order of asking for vote, it shall be first for support, next for opposition, and last for abstinence.

## 20. የማሻሻያ ሀሣብ ስለማቅረብ

1. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል በውይይት ላይ ባለ የውሣኔ ሀሣብ ላይ የማሻሻያ ሀሣብ በጽሑፍ ወይም በቃል ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የምክር ቤቱ ሰብሳቢ በቃል የቀረበውን የማሻሻያ ሀሣብ አቅራቢው የማሻሻያ ሀሣቡን በጽሑፍ እንዲያቀርብ ማድረግ ይችላል፡፡
3. የማሻሻያ ሀሣቡ በውይይት ላይ ያለው ጉዳይ አካል ሆኖ ሊወሰድ የሚችለው በመጀመሪያ ጉዳዩን ያቀረበው አባል ሲቀበለው ብቻ ነው፡፡
4. በማሻሻያ ሀሣብ ላይ የማሻሻያ ሀሣብ ማቅረብ ይቻላል፤ ሆኖም ከአንድ በላይ የማሻሻያ ማሻሻያ ሊቀርብ አይችልም፡፡

## 20. Proposing Amendment

1. Any member of the council may propose an amendment, orally or in writing, on the motion under discussion.
2. When the chairperson finds it essential, he may cause the initiator to present his oral amendment in writing.
3. The amendment can be taken as part of the topic under discussion on condition that the member who raised the issue first agrees.
4. It is possible to propose an amendment on another amendment; however, more than one amendments may not be proposed.

## 21. ሀሣብን የማንሣት መብት

1. ለውይይት ሀሣብ ወይም የማሻሻያ ሀሣብ ያቀረበ አባል በጉዳዩ ላይ ድምጽ ከመሰጠቱ በፊት ያቀረበውን ሀሣብ ለማንሣት ይችላል፤ ከዚህ በኋላ በጉዳዩ ላይ የተጀመረ ውይይት

## 21. The Right of Withdrawing One's Opinion

1. Any member who has proposed a motion or an amendment can withdraw the proposal he has put forward before; then after, the discussion, if any, already

www.abyssinialaw.com



ቢኖር ይቆማል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው ቢኖርም የቀረበው ሃሳብ ወይም የማሻሻያ ሃሳብ ይገፋበት ዘንድ ከተጠየቀና አንድ ሦስተኛ የሚሆኑትን ሌሎች የምክር ቤት አባላት ድጋፍ ካገኘ ውይይቱ ሊቀጥል ይችላል::

## 22. በውይይት ወቅት መኖር ስለሚገባው ሥነ-ምግባር

በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ የሚደረገው ማናቸውም ውይይት:-

ሀ/ በአባሎቹ መካከል ሊኖር በሚገባው መልካም ሥነ-ምግባርና የመከባበር መንፈስ ላይ የተመሠረተ እና

ለ/ ለምክር ቤቱ ከቀረበው ጉዳይ ጋር የተያያዘና አግባብነት ያለው መሆን አለበት::

## 23. ውይይት ስለማቆም

1. ምክር ቤቱ በአንድ ጉዳይ ላይ በሰፊው ከተወያየበት በኋላ ሰብሳቢው ወይም ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል ውይይቱ ቆሞ ድምጽ እንዲሰጥበት ሀሣብ ሊያቀርብ ይችላል::
2. ውይይቱ እንዳይቆም ተቃዋሚ ካለ ምክር ቤቱ ያለውይይት በድምጽ ብልጫ ይወስናል::

## 24. ድምጽ የሚሰጥባቸው ጉዳዮች ቅደም ተከተል

ውይይት በተደረገበት ጉዳይ ላይ ድምጽ የሚሰጠው በሚከተለው ቅደም ተከተል

started upon the issue, shall stop.

2. Without prejudice to the provision of sub-article 1 of this article, if it is required to go on discussing on the proposal or amendment, and gets approval of one-third of other members, the discussion may continue.

## 22. Decorum During Discussion

Any discussion conducting at the meeting of the council shall be:

a. based on good conduct and spirit of reciprocal respect among members of the council;

b. appropriate and relevant to the topic submitted to the council.

## 23. Stopping Discussion

1. The chairperson or any member of the council may propose the stoppage of a discussion on an issue, and a vote after the council has discussed it in detail.
2. If there is an opposition to the stoppage of the discussion, the council shall take a decision by majority vote without any further discussion.

## 24. Sequence of Issues to Vote on

In order to take a vote on an issue dealt with, the sequence shall be the following:

www.abyssinialaw.com



ይሆናል፡-

ሀ/ ጉዳዩ ነጥብ በነጥብ በሚታይበት ጊዜ ስለአንድ ቃል፣ ሐረግ፣ አረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ የቀረቡት የማሻሻያ ሀሣቦች ከሁለት በላይ ሲሆኑ ከጉዳዩ በራቀው በመጀመር፤

ለ/ በቀረበው ጉዳይ በእያንዳንዱ ነጥብ ላይ እና

ሐ/ በጉዳዩ በጠቅላላው::

a. start with the remoter amendment when more than one amendments are proposed about a word, a phrase, a sentence or a paragraph in going through the issue point by point;

b. on each point of the presented topic;

c. on the issue generally.

## 25. የውሣኔ አሰጣጥ

1. ምክር ቤቱ ማናቸውንም ጉዳይ በተባበረ ድምጽ ይወሰናል፤ በተባበረ ድምጽ መወሰን ካልቻለ በስብሰባው ላይ በተገኙ አባላት በድምጽ ብልጫ ይወሰናል::
2. ድምጽ እኩል ለእኩል የሆነ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ወሣኝ ድምጽ ይኖረዋል::
3. የድምጽ አሰጣጡ ሥርዓት በይፋ እጅ በማውጣት ወይም በምስጢር እንዲሆን ምክር ቤቱ እንደአስፈላጊነቱ ሊወስን ይችላል::
4. እንደአስፈላጊነቱ ድምጽ ከተሰጠ በኋላ የም/ቤቱ አባላት ድምጽ የሰጡበትን ወይም ያልሰጡበትን ምክንያት በአጭሩ በጽሑፍ ወይም በቃል የማብራራት እድል ሊሰጣቸው ይችላል::
5. ምክር ቤቱ ውሣኔ በሰጠበት ጉዳይ ላይ በድምጽ ብልጫ እንደገና ውይይት ማካሄድ ይቻላል፤ ሆኖም ቀደም ሲል የተላለፈው ውሣኔ ሊለወጥ የሚችለው በስብሰባው ላይ በተገኙት አባላት ሁለት ሦስተኛ ድምጽ ድጋፍ ሲያገኝ ነው::

## 25. Decision Making

1. The council shall pass a motion by a unanimous vote; if it cannot do so, it shall decide by the majority vote of members present.
2. Where the vote draws in a tie, the motion favored by the chairperson shall have a decisive vote.
3. The council may decide, as it may be required, the manner of voting to be either by official hand raising or in secrecy.
4. As it may be necessary, members of the council may be given a chance to clarify the reason, in brief orally or in writing, why they have or not voted.
5. The council may reconsider a discussion on an issue already decided by the majority vote; nevertheless, the passed decision can be changed if only it gets the approval of two-third of the members in attendance.

www.abyssinialaw.com



# ክፍል አምስት
# የምክር ቤቱ ውይይትና ውሣኔዎች ምስጢር ስለመሆናቸውና ስለቃለ-ጉባዔ

## 26. የምክር ቤቱ ውይይትና ውሣኔ ምስጢር ስለመሆኑ

1. በዚህ ደንብ መሠረት እንዲሳተፉ ከተፈቀደላቸው ሰዎች ወይም ምክር ቤቱ ካልፈቀደ በቀር የምክር ቤቱ ስብሰባ ለማንኛውም ሰው ክፍት አይሆንም::
2. ምክር ቤቱ የሚያደርገው ውይይት በምስጢር መያዝ አለበት:: የምክር ቤቱ ውሣኔም ተፈርሞ ለሚመለከታቸው ወጪ እስከሚደረግ ድረስ በምስጢር መጠበቅ ይኖርበታል:: ሆኖም የዚህ ድንጋጌ ኃይለ ቃል ጉዳዩ የሚመለከታቸው ቢሮዎችና ሌሎች አስፈፃሚ አካላት ውሣኔውን ተከታትለው በሥራ ላይ እንዳያውሉ የማገድ ውጤት አይኖረውም::
3. ማንኛውም የምክር ቤቱ ውሣኔ ለሚመለከተው አካል በጽሑፍ ይተላለፋል::
4. ሰብሳቢው አስፈላጊ መሆኑን ሲያምንበት የም/ቤቱ ውሣኔ ለዜና ማስራጫ ክፍሎች ሊገለጽ ይችላል::
5. ለሕዝብ ጥቅምና ለክልሉ ደህንነት ሲባል በልዩ ሁኔታ በምስጢር እንዲያዙና ከተፈቀደላቸው አካላት ውጭ በይፋ እንዳይሰራጩ ከታገዱት ውጭ ያለ ማናቸውም የምክር ቤቱ ውሣኔ ሠነድ ለሕዝብ ክፍት ይሆናል:: ዝርዝር አፈፃፀሙ በጽ/ቤቱ ኃላፊ በሚወጣ የውስጥ መመሪያ ይወሰናል::

# PART FIVE
# SECRECY OF DISCUSSION AND DECISION OF THE COUNCIL AS WELL AS MINUTES

## 26. Secrecy of Discussion and Decision of the Council

1. Except those people who are allowed by this regulation or by the will of the council to take part, any meeting of the council is conducted behind closed doors.
2. The discussion the council undertakes shall be kept secret. Likewise, the decision of the council shall be secret until it is signed and handed out to concerned organs. Provided, however, that the command of this provision shall not have a preventive effect upon concerned bureaux and other executive organs to follow up and implement the decision.
3. Any decision of the council shall transfer to a concerned body in a printed form.
4. When the chairperson believes in its necessity, the decision of the council may be revealed to newscasts.
5. Any decision documents of the council shall be accessible to the public regardless of any decision of the council except those documents to be kept secret, or banned for the sake of public benefit and regional security from revealing to none but to permitted bodies.

www.abyssinialaw.com



## 27. ስለቃለ-ጉባዔ

1. የምክር ቤቱ ስብሰባ ቃለ-ጉባዔ ተናጋሪዎችን በስም በመጥቀስ የስብሰባውን ውይይትና ውሣኔዎች በዝርዝር ገልጾ በሚያሳይ ሁኔታ ይይዛል፤ በቴፕና አስፈላጊም ሲሆን በፊልም ይቀረፃል፡፡

2. የምክር ቤቱ ስብሰባ ቃለ-ጉባዔ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-
   - ሀ/ የስብሰባውን ቦታ ቀንና ሰዓት፤
   - ለ/ በስብሰባው ላይ የተገኙትን አባላት ዝርዝር፤
   - ሐ/ በስብሰባው ላይ ያልተገኙትን አባላት ዝርዝርና ያልተገኙበትን ምክንያት፤
   - መ/ በስብሰባው ላይ የተገኙ ሌሎች ሰዎች ካሉ ስማቸውንና የተገኙበትን ምክንያት፤
   - ሠ/ ለስብሰባ የቀረበውን አጀንዳ፤
   - ረ/ የስብሰባው ውይይትና እንዲመዘገብ የተጠየቀን የሀሣብ ልዩነት፤
   - ሰ/ በስብሰባው ላይ የተላለፉት ውሣኔዎች፤
   - ሽ/ በምክር ቤቱ በተለየ ሁኔታ ተወስኖ ከሆነ ለውሣኔው አፈፃፀም የተሰጠውን ጊዜና አፈፃፀሙን ለመከታተል ኃላፊነት የተሰጠውን የሥራ ክፍል ወይም የሥራ ኃላፊ እና
   - ቀ/ ስብሰባው የተፈፀመበትን ሁኔታና ሰዓት፤

3. የምክር ቤቱ ስብሰባ ቃለ-ጉባዔ በም/ቤቱ ከፀደቀ በኂላ በሰብሳቢውና በጽ/ቤት ኃላፊው ወይምእርሱ በሚወክለው ሰው ፊርማ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 27. Minutes

1. Minutes of the meeting shall be recorded in such a way that they show the council's decision and discussion in detail mentioning the speakers in name, it shall also be recorded by a tape or, if need be by a video.

2. Minutes of the meeting of the council shall comprise the following:
   - a. venue, date and time of the meeting;
   - b. list of members present;
   - c. list of members absent and the reason for their absence;
   - d. names of other persons, if any, and the reason for their presence;
   - e. the agenda submitted for the meeting;
   - f. discussion of the meeting and opinion differences requested to be registered;
   - g. decisions passed in the meeting;
   - h. if decided in a specified manner, the time fixed for the execution of the decision, and the work unit or head of the unit assigned the responsibility of monitoring the execution,;
   - i. condition and time of completion of the meeting.

3. Minutes of the meeting of the council, after being approved by the council, shall also be approved by the chairperson and the head of the office or his representative.

www.abyssinialaw.com



4. ማንኛውም አባል የምክር ቤቱን ስበሰባ ቃለ-ጉባዔ ለማገናዘብ ሲፈልግበጽ/ቤቱ ኃላፊ አማካኝነት ለማየት ይችላል::

4. Whenever any member wishes to crosscheck the minutes of the meeting, he can have a look at it through the head of the office.

## ክፍል ስድስት
## ስለኮሚቴዎች

## PART SIX
## THE COMMITTEES

### 28. ቋሚ ኮሚቴዎችን ስለማቋቋም

ምክር ቤቱ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑትን ቋሚ ኮሚቴዎች ሊያቋቁም ይችላል::

### 28. Establishment of the Standing Committees

The council may establish standing committees necessary for its duties.

### 29. ስለምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች አይነትና ጥንቅር

በዚህ ደንብ አንቀጽ 28 መሠረት የሚቋቋሙት ኮሚቴዎች ዓይነት፣ ብዛት፣ ያባላት ጥንቅርና የሥራ ድርሻ ይህንን ደንብ ተከትሎ በሚወጣ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ይገለፃል::

### 29. Types and Composition of the Standing Committees of the Council

The type, number, composition and job allocation of the committees to be established in accordance with article 28 of this regulation shall be explained by the directive to be issued following this regulation.

### 30. ስለጊዜያዊ ኮሚቴዎች

ምክር ቤቱ:-

ሀ/ ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ሊያቋቁምና

ለ/ የምክር ቤቱ አባላት ያልሆኑ ሰዎች የጊዜያዊ ኮሚቴዎች አባላት ሆነው እንዲሠሩ ለማድረግ ይችላል::

### 30. Provisional Committees

The council may

a. set up provisional committees when it is found necessary for its task.

b. have persons who are not member act as member of the council.

### 31. ስለአገልግሎቶች

የምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት ለምክር ቤቱና ለልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ሥራ ክንዋኔ አስፈላጊ የሆነውን አገልግሎት ይሰጣል::

### 31.The Services

Office of the council shall render the necessary service to the council and various committees to foster their activities.

www.abyssinialaw.com



# ክፍል ሰባት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 32. ደንቡ ስለሚፀድቅበት ሁኔታ

ይህ የውስጥ ደንብ በምክር ቤቱ አባላት ሁለት ሦስተኛ ድምጽ ከተደገፈ ይፀድቃል::

## 33. ደንቡን ስለማሻሻል

ይህ የውስጥ ደንብ በምክር ቤቱ አባላት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ውሣኔ ሊሻሻል ወይም በሌላ ሊተካ ይችላል::

## 34. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ርዕሰ መስተዳድሩ ለዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች በየጊዜው ሊያወጣ ይችላል::

## 35. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከህዳር 13 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህር ዳር

ህዳር 13 ቀን 1995 ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልል

ርዕሰ መስተዳድር

# PART SEVEN
# MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 32. Effective Condition of the Regulation

This inhouse regulation shall be effective if approved by two-third members of the council.

## 33. Amending the Regulation

This internal regulation can be amended or replaced with another altogether by two-third vote decision of the council members.

## 34. Power to Issue Directives

Head of the government may issue detailed directives necessary for complete execution of the provisions hereof.

## 35. Effective Date

This regulation shall enter into force as of Nov. 22nd, 2002.

Done at Bahir Dar

This 22nd day of Nov. 2002

YOSEF RETTA

Head of Government of the Amhara

National Regional State